# እድገት ብሎ ውሸት

**ዶር አክሎግ ቢራራ**

**“የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚታወቀው ከላይ ወደታች በሆነ የእዝና የቁጥጥር መርሆ ነው”**

**The Economist, March 12, 2016**

“ከብዙ ቢሊዮን ዶላር እርዳታ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ፤ የዛሬ ሃያ አምስት አመታት በፊት ከነበረው አልተሻሻለም”

The Economist, Summer 2010

“የአእምሮና የመንፈስ ችግር አለብን? በአእምሮና በመንፈስ ኃይሉ የማይጠቀም ሕዝብ አህያ ከመንዳት ሊወጣ አይችልም።”

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም--የክሕደት ቁልቁለት

አገራችን ኢትዮጵያ ዘርፈ-ብዙ ችግሮች እንዳሉባት ከላይ ያቀርብኳቸው ጥቅሶች ያካትቱታል። ከሁሉም በላይ “የአአምሮና የመንፈስ ችግር” ስር ሰዶ ሕዝቡን ሽባ ማድረጉ ለችግሮቻችን ሰው ሰራሽ የሆነ ማህበረሰባዊ ውድመት መሰረት ሆኗል። በፖለቲካው፤ በአገዛዙ፤ በማህበረሰባዊ አስተሳሰቡና አመለካከቱ፤ በኃይማኖቱና በኢኮኖሚው፤ በውጭ ግንኙነቱና ሌላው ጠለቅ ብሎ ሲታይ ጠባብ **<u>ዘረኛነትና</u>** ጎሰኛነት ሕዝቡን ለእርስ በርስ ግጭት፤ ለድህነትና ለስደት፤ አገሪቱን ለመከፋፈልና ለጥፋት ዳርጓቸዋል። የዚህ ሃተታ መሰረታዊ ሃሳብ ዘረኛነትና ጠባብ ጎሰኛነት መፍትሄ ካላገኙ አደጋው እየተባባሰ ይሄዳል የሚል ነው። የፈለገውን ያህል የአስተዳደር ብልሺትና በደል፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ስርዓታዊ ሆነዋል የሚል ትችት በያቅጣጫው ቢሰነዘርና የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ይህን ቢያምኑም የችግሩን መንስኤ፤ ማለትም፤ ጠባብ ዘረኛነትንና ጎሰኛነትን ለመተቸትና ለመፍታት ካልቻሉ አፋኙ፤ አግላዩ፤ ኪራይ ሰብሳቢውና ሙሰኛው ስርዓት ይቀጥላል። ድርብ አሃዝ ተብሎ የሚለፈፈው የእድገት መጠን ይቀንሳል። ለሰብአዊ አገልግሎትም ሆነ ለልማት የሚሰጠው ግዙፍ የውጭ እርዳታ ችግሩን አይፈታውም። በሌሎች አገሮች የሆነውን መሰረት አድርገን አግባብ ያለው መልስ ለመስጠት ብንሞክር ጥገኝነት ሁኔታውን ያባብሰዋል። ተከታታይ የድርቅ ረሃብ ምሳሌ ነው።

በያዝነው ወር የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ተራድዖ ድርጅት የኢትዮጵያን የድርቅ ረሃብ አስከፊነት አስመልክቶ ያወጣው ዘገባ ተከታታይ የሆነው ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል? የሚለውን ጥያቄ እንዳነሳ አስገድዶኛል። በአጭሩ፤ የምግብ የአደጋ ድጋፍ በአስቸኳይ የሚያስፈልገው ህዝብ **<u>ቁጥር 10.2</u>** ሚሊየን፤ የምግብ እርዳታ በዘላቂነት የሚያስፈልገው **<u>2.6 ሚሊየንና</u>** ወደፊት የምግብ ድጋፍ የሚያስፈልገው **<u>5.8 ሚሊየን፤</u>** በጠቅላላ **<u>18.6 ሚሊየን</u>** (ከአገሪቱ 101 ሚሊየን ሕዝብ 17-18 በመቶ) መሆኑ ነው። “በአፋርና በሶማሌ ክልሎች በስጋት የሚኖሩ ቤተሰቦችና ዘላኖች ቢያንስ እስከሚቀጥለው መስከረም ድረስ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። በተጨማሪ፤ በሃረርጌ (ኦሮምያ ክልል)፤ በሰሜን ወሎ (አማራ ክልል) የተጎዱት ተመሳሳይ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ከመጋቢት 16–19, በዩኤስኤድ ዲሬክተር በጀረሚ ኮኒንዲክ  የተመራው ቡድን ወደ ትግራይ ክልል ተጉዞ “በምስራቅ አማራ እና ትግራይ፤ በደቡብ ብሄር፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሰሜናዊ ቀጠናና በምስራቅ ኦሮምያ አስከፊ ረሃብ እንዳለ፤ እንስሳዎች እንዳለቁ፤ የምግብ ዋጋ ግሽፈት አስጊ ደረጃ ላይ እንደደረሰ፤ ቤተሰቦች ያላቸውን ገቢ ለምግብ አውጥተው የቀረ ገንዘብ እንደሌላቸውና የረሃቡ ሁኔታ **<u>ክራይሲስ ወይንም ጠንቅ</u>** ከሚያሳይ ደረጃ (Crisis-level) ላይ” መድረሱን አስምረውበታል። ረሃብ ሁሉን ሕዝቦች በክሏል። ይህ ብቻ ሕዝቡን ሊሰበስበው ይችላል የሚሉ ታዛቢዎች በየቦታው አሉ።

በዚህ ወር አጋማሽ፤ “በአማራ፤ በአፋርና በኦሮምያ ክልሎች ቢያንስ **<u>ወደ አንድ ሚሊየን የሚገመቱ</u>** ኢትዮጵያዊያን የሚጠጡት ውሃ” እንደሌላቸውና የሚመኩት አስተማማኝ ባልሆነ በመኪና በሚጓጓዝ የውሃ ድጋፍ መሆኑን ገልጸዋል። በተመሳሳይ፤ በደቡብ፤ በሶማሌና በትግራይ ክልሎች ብዙ ኢትዮጵያዊያን “የመጠጥ፤ የመጸዳጃና የጤና አገልግሎት ውሃና ሌላ አስፈላጊ የሚያገኙት በመጓጓዣ መኪናዎች” መሆኑን፤ “የአስቸኳይ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸውና ትኩረት ከተሰጣቸው **<u>166 አውራጃዎች</u>** መካከል ድጋፍ የሚያገኙት **<u>105</u>** ሲሆኑ፤ **<u>ሌሎች 33 አውራጃዎች</u>** ድጋፍ የሚያገኙት የመንግሥት ካልሆኑ የውጭ የበጎ አድራጎት ተቋሞች መሆኑን” ገልጿል፡፡ ከእነዚህ **<u>28 አውራጃዎች</u>** “ምንም አይነት አገልግሎት አያገኙም።” ዘገባው ከተቻቸው ማነቆዎች መካከል ፈጣን መሰረተ ልማት ተካሂዷል በሚባልባት ኢትዮጵያ አሁንም በአንዳንድ ክልሎች “መሰረተ ልማት፤ መንገድ ወዘተ፤ አለመኖሩና ነዋሪዎች አገልግሎት ለማግኘት እርቀትቱን ለመወጣት አለመቻላቸው ነው፤ በተለይ በአማራው ክልል።” በክልሎች መካከል መሰረተ ልማት፤ መንገድና ሌላ የተዛባ መሆኑን ያሳያል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? የሚለውን ሕዝብ ይመልሰው።

የድርቅ ረሃብ ሲከሰት በተለየ የሚጎዱት ለመንቀሳቀስና ሌሎች አማራጮች ለመፈለግ አቅም የሌላቸው ኢትዮጵያዊያን ናቸው---ህጻናት፤ እርጉዝና የሚያጠቡ እናቶች፤ እድሚያቸው የገፋ ዜጎች፤ አይነስውሮች። የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ድርጅት **<u>“ለ450,000</u>** ህጻናት፤ ለእርጉዞችና ልጆች ለሚያጠቡ እናቶች የእለት ምግብ እርዳታ ይለግሳል።” ህጻናት በምግብ እጥረት የተነሳ የወደፊት እድገታቸው እንደሚበከል ጥናቶች ያሳያሉ። “የኢትዮጵያ መንግሥት እንደሚለው በሚቀጥሉት ወራቶች ይህ ድርጅት እነዚህን የመሰሉት ወገኖቻችን ከጠንቁ እንዲወጡ **<u>ለማስቻል በ135</u>** የመመገቢያ ጣቢያዎች፤ ትኩረት ለሚሰጣቸው በአንደኛ ደራጃ በሁለተኛ ደረጃ ለተመደቡ ወረዳዎች፤ በግምት **<u>ለ506,000</u>** አደጋ አፋፍ ላይ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የምግብ አገልግሎት እንደሚሰጥ” ይጠበቃል። ይህ ጠንቅ

ብዙ የገንዘብ ወጭ ይጠይቃል። ልክ እንዳለፈውም ባይሆን፤ የኢትዮጵያ ወዳጅ አገሮች ድጋፍ ሰጥተዋል፤ ወደፊትም ይሰጣሉ የሚል ግምት አለ። ጥናቱ እንደገመተው እስከሚቀጥለው መስከረም ያለውን፤ ቢያንስ **የ17 ሚሊየን (ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከአስራ ሰባት በመቶ በላይ የሚገመቱ) ረሃብተኞችን** ችግር **ለመወጣት $1.48** ቢሊየን ድጋፍ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ይኼን ወጭ ለማሟላት አይችልም። የእድገቱ ውጤት በጥቂቶች መማረኩን ያሳያል።

እስካሁን፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ካለው የተወሰነ **ገቢ $381 ሚሊየን** ወጭ አድርጓል። ይህ ነፍስ ለማዳን የተደረገ ፈሰስ የማይናቅ አስተዋፆ ነው። ገዢው ፓርቲ የችግሩን ግዙፍነትና የራሱን አቅም ደካማነት ቢቀበል የበለጠ ያስመሰግነው ነበር። ሆኖም፤ ችግሩንና ድክመቱን ተቀብሎ አያውቅም። ችግርን ለምፍታት ሌላ ችግር የሚፈጥር አገዛዝ ነው። ስለሆነም፤ አከራካሪው ነጥብ ኢትዮጵያ ለምን ከዚህ ደረሰች፤ እድገት አለ እየተባለ፤ ሊወገድ የሚችል ጠንቅ ለምን ሊቀረፍ አልቻለም? ነው እንጅ አሁን ነፍስ ለማዳን የሚደረግ ጥረት የለም የሚለው አያዋጣም። ቢያንስ ቢያንስ መቀበል የሚኖርብን በኢህአዴግ ውስጥም ክብርና ዝና፤ ህሊንናና ታሪክ የሚባል ጉዳይም እኮ አለ። ለወገኖቻቸው የሚቀረቀሩ አሉ።

"የአእምሮና የመንፈስ ኃይላችን" መጠቀም ካቆምን ሃያ አምስት ዓመታት አልፎናል። የራሳችን ምሁራኖቻችና የራሳችንን ሕዝብ አናምንም፤ አናከበርም። የምናከብረውና የምንጠቅሰው የውጭ ሰዎችንና ተቋሞችን ሆኗል። ስርዓቱም የሚፈልገው ይኼን ነው። በራሳችን ፈጠራና የማምረት ችሎታ እንዳንተማመን፤ ራሳችን እንዳንችል ውዝንብር አለ። ውዝንብር ለጠባብ ዘረኞነትና ለኪራይ ሰብሳቢነት ይረዳል። ውዝንብር ለማፈን ይረዳል። ውዝንብር ሕዝብን ከሕብ ጋር ለማጋጨት ይረዳል ወዘተ። የውጭ እርዳታን ሚና የማየው ከዚሁ የጥገኝነትና ውዝንብር አንጻር ጭምር ነው። ለምሳሌ፤ በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ከጥገኝነት የምትወጣ መቸ ነው? ብለን ብንጠይቅ ትክክለኛ መልስ የሚሰጥ ባለሥልጣን አናገኝም፤ ካለ የሚናገረው አስተማማኝ አይደለም።

እንደተለመደው ከፍተኛውን የምግብ እርዳታ የለገሰው የአሜሪካ መንግሥት ነው። ከ2015-2016 ባለው ጊዜ **$546 ሚሊየን ለግሷል።** የአውሮፓ የአንድነት ድርጅት **$106 ሚሊየን፤** እንግሊዝ **$87 ሚሊየን፤**ጀርመኒ **$45 ሚሊየን፤** ስዊድን **$29 ሚሊየን**፤ ጃፓን **$28 ሚሊየን፤** ሆላንድ **$17 ሚሊየን**፤ ካናዳ **$16 ሚሊየን፤** ሰዊትዘርላንድ፤ **$15 ሚሊየን** የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች ስብስብ $**39 ሚሊየን** ሚሊየን ለግሰዋል። ሌሎችም እንደለገሱ ይነገራል። እነዚህ ለጋሶች በተደጋጋሚ ለተከሰቱ ጠንቆች ከመለገሳቸው ባሻገር ለጠንቁ ምክንያት የሆኑትን ማነቆዎች ነክተዋቸዋል ለማለት አይቻልም። ለምሳሌ የመሬት ስሪት፤ አጠቃቀምና ነጠቃን አይነኩም። ዘረኞነት አጥፊ መሆኑን ቢያውቁትም እንደ ፖለቲካ ኮረንቲ ያዩታል። እነዚህንና ሌሎችን የስርዓት ጉድለቶች የአሜሪካው ዘገባም አልነናካቸውም። የፖለቲካውንና የፖሊሲውን ጉዳይ ለመንካት የማይችለው ዘገባ  የሚለው "ድርቅ ለኢትዮጵያዊያን ህይወት አደጋን ቢፈጥርም፤ የገበሪዎች፤ የዘላኖችና ሌሎች የገጠር ነዋሪዎች ህይወት በተከታታይ የሚዛባው በየጊዜው በሚከሰቱ ጎርፎች፤ የአገር ውስጥ በተፈጥሮ ኃብት ላይ በሚካሄዱት **የእርስ በርስ ግጭቶች፤** ጎጅ በሆኑ የምግብ ዋጋ ግሽበቶች፤ አግባብ በሌላቸው የመሬት አጠቃቀም ዘዴዎች፤ በእህል በሽታዎች፤ በጤንነት አገልግሎት ጉድለቶች ወዘተ" ነው ብሏል። እነዚህ ሁሉ አግባብ ያላቸው ትችቶች ናቸው። ግን በቂ አይደሉም።

መሰረታዊው ራስን ያለመቻል ችግር እንዴት እንደሚፈታና ባለፉት አስር እስከ አስራ ዓምስት ዓመታት በተከታታይ በየዓመቱ ድርብ አሃዝ እድገት አሳይታለች የምትባለው ኢትዮጵያ ጠንቁን እንዴት ለማስወገድና ለመቋቋም እንዳልቻለች አይተችም። ድርብ አሃዝ እድገት እውነት ነው ከተባለ የተፈጥሮውን ችግር ለመቋቋም አቅም አለ ማለት ነው። ይኼን ለማመን ከሚያስቸግረው፤ ስኬታማ ሆኗል ከሚባለው ከአገሪቱ ጠቅላላና የነፍስ ወከፍ ገቢ አንጻር እንየው። ልዩ ልዩ ዘገባዎች የተለያዩ መረጃዎች ይሰጣሉ፤ ሲአይኤ የሚለው ከዓለም ባንክ ይለያል፤ ኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ የሚለው ከዓለም ባንክ ይለያል፤ ሁሉም የሚሉት ከኢትዮጵያ መንግሥት ይለያል። ስለዚህ የኢትዮጵያን የእድገት መጠን፤ የአገር ጠቅላላና የነፍስ ወከፍ ገቢ በትክክል ለማወቅ አይቻልም። በአንድ ወቅት ከአንድ ካድሬ ጋር በሬድዮ ስንወያይ፤ "እድገቱን ለመመዘንና ለመተቸት **አዲስ አበባ ቃተኛ ለመግዛት** የሚሰለፈውን ሕዝብ ቢያዩት ጥሩ ነበር" አለኝ። እኔም ገርሞኝ በአዲስ አበባ ከተማ ከቆሻሻ ለቅመው የሚበሉትስ ህይወት የላቸውም ማለት ነው?" የሚል ጥያቄ አቅርቤ ሳንስማማ ተለያየን። የእድገቱን መጠን ለማወቅ የማይቻልበት ዋና ምክንያት ግልጽነት ስለሌለ ነው። ግልጽነት ካለ የመንግሥት ተቆርቋሪነት፤ ተጠያቂነትና ሃላፊነት አለ ማለት ነው። እነዚህ መርሆዎች ቢኖሩ ኖሮ ጠባብ ዘረኛነትና ጎሰኛነት ህብረተሰቡን አይበክሉም ነበር። ሕዝቡ በልቶ ያድር ነበር። ኪራይ ሰብሳቢነት ይቀንስ ነበር ወዘተ ወዘተ።

በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ህዝብ አሰቃቂ ኑሮ አንጻር ሳየው ውጤቱ "እመኑኝ ተብሎ የማይታመን" መረጃ (Make-believe economics that can't be trusted)  መሆኑን ያንጸባርቃል። የኢኮኖሚውን ውጤት ለማመን የሚያስቸግርበት ምክንያት እንዲህ ነው። የአገሪቱ ጠቅላላ ገቢ በአስተማማኝ መረጃ የተደገፈ አይደለም፤ በ**1994 $7 ቢሊየን** የነበረው በ**2006 $15 ቢሊየን ከዚያ** በሁለት ዓመታት፤ ማለትም በ2008 **$27 ቢሊየን፤**  እንደገና በሁለት ዓመታት በ**2010 $30 ቢሊየን፤** አሁንም በሁለት ዓመታት በ 2012 **$43** እና በ2014 $56 ቢሊየን እያለ ይጨምራል። በ**2006 የነፈስ ወከፍ ገቢዋ በአመት $194 የነበረችው አገር** በያመቱ እየናረ ሄዶ በ**2014 ወደ $573** ተሸጋገረ ተባለ። ገዢው ፓርቲ በራሱ የፖለቲካ ውሳኔ መሰረት ጠቅላላ ገቢዋ አንዳንዴ **በሶስት ዓመታት** ከእጥፍ በላይ የሆነባት ብቸኛ አገር ሆናለች ብሎ ዓለምን አሳመነ፤ ቢያንስ ለማሳመን ሞከረ። ይኼን ካለ በኋላ አሁን የምግብ እርዳታ ይጠይቃል። አበዳሪዎች፤ ለጋሶች፤ ኢንቬስተሮችና ወዳጅ አገሮች እድገቱን ተቀበሉ። በመረጃ ማጭበርበር ልምድ ስለሆነ የአገሪቱ ጠቅላላ ገቢ አሁንም እመርታዊ በሆነ ደረጃ **በ2015** መጨረሻ የኢትዮጵያ **ጠቅላላ ገቢ$58 ቢሊየን** **ደርሷል ተባለ። በ2006 $56** ቢሊየን ነበር የሚለውን ከተቀበልን የመጨረሻው የሲአይኤው ስሌት የሚያከራክር አይመስለኝም። እንዲህ እያለ የእድገቱ መጠን ታይቶ የማይታወቅ፤ በዓለም "ተወዳዳሪ

የሌለው” ሲባል ቆየ። ሰሞኑን አይኤምኤፍ ባወጣው ስሌት የአገሪቱ እድገት ከድርብ አሃዝ ወደ **4.5 በመቶ** ያቆለቁላል ተባለ። የእድገቱ ውጤት በጥቂቶች እየተማረከ ከቀጠለ የእድገቱ ማቆልቆል ለታራው ኢትዮጵያዊ ህይወት ለውጥ አያመጣም።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የገጠር ስለሆነ ከላይ የተጠቀሱት አሃዞች ከገጠሩ ሕዝብ ገቢና ኑሮ መሻሻል ጋርም መያያዝ አለባቸው። The Economist, በ March 12, 2016, ስለ አፍሪካ አገሮች የእርሻ እድገት **ባደረገው የ2000-2014** ዘገባ አገሮችን እያነጻጸረ እንዲህ ይላል። “አንድ የሩዋንዳ ገበሬ የሚያርሰውን ግማሽ ሄክታር መሬት አሻሽሎ፤ የራሱን ቤተሰብ የምግብ ፍላጎት ካሟላ በኋላ በወር ሁለት ጊዜ ስጋ ለመግዛት ችሏል። በተጨማሪ ምርቱን ሸጦ **በባንክ ቁጠባ $230** ያስቀምጣል።” የተፈጥሮና ሌላ ችግር ቢከሰት ቤተሰቡን ለመመገብ ይችላል። የተባበሩት መንግሥታት የእርሻ ድርጅት ባደረገው ጥናት መሰረት በየእርስ በርስ እልቂት የምትታወቀውና በጅኦግራፊ ትንሿ ሩዋንዳ በ2014 መጨረሻ በ2000 ዓ.ም. ካመረተችው እጥፍ አድርጋ **792,000 ቶን** እህል አምርታለች” ይላል። በተመሳሳይ ኢትዮጵያም በዚህ ወቅት “ምርቷን ሶስት ጊዜ” ማሳደጓን ይናገራል። ይህን እድገት ማስታረቅ ያለብን ኢትዮጵያ **በ2012 750,000** ሜትሪክ ቶን ስንዴ ከአርጀንቲናና ከራሺያ ከመሸመቷና **300,000** ሜትሪክ ቶን ስንዴ በእርዳታ ከአሜሪካ ከመለገሷ ጋር ነው። በ2013 ብቻ አሜሪካ **500,000** ቶን ስንዴ ለግሳለች። ለማስታወስ፤ ከደቡብ አፍሪካ ቀጥላ፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የስንዴ አምራች አገር ናት። ራሷን ለመቻል እምቅ አቅም አላት ማለት ነው። ሆኖም፤ **98** በመቶ የሚሆነውን እህል የሚያመርቱት የተሻሻለና ለመሬቱ ተስማሚ የሆነ ዘር የሚጠቀሙት ዝቅተኛ **ገበሬዎች 8** በመቶ ብቻ ናቸው። ዘጠና ሁለት በመቶው የሚጠቀመው መሳሪያ የጥንት መሆኑ ነው። የማዳበሪያ የብድር ግብዓት የሚጠቀሙም ዝቅተኛ መሆናቸው ይገመታል።

የመሬት ስሪትና ግብዓቶች ከተሻሻሉ ምርት ማደጉ አያከራክርም። ከላይ ለናሙና የቀረቡትን ምርት ውጤት ስኬታማ ያደረጉት ዝቅተኛ አምራች ገበሬዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ ለውጭ አምራቾችና ነጋዴዎች መሬትን መስጠት ጉዳት እንዳለው ያሳያል። በአፍሪካ “ሁለት ሶስተኛው የእርሻ መሬት” ከአንድ ሄክታር በታች ነው። በኢንቬስተሮች የተያዘ የንግድ እርሻ ብዙ መሬት መጠቀምን ይጠይቃል። በዝቅተኛ ገበሬዎች የሚታረሰው መሬት ዝቅተኛ ከሆነ እድገቱ እንዴት ተሳካ? ብለን ብንጠይቅ ስሪቱን፤ ግብዓቱንና አጠቃቀሙን በማሻሻል የሚል መልስ እናገኛለን። የመስኖን እርሻ በማስፋፋት የሚል መልስ እናገኛለን። ታይላንድና ሌሎች አገሮች እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ለዚህ የሚጠቅሙት ግብዓቶች አግባብ ያለው የመሬት ስሪት የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። በተጨማሪ ለአገሩና ለመሬቱ ተስማሚ የሆነ ማዳበሪያና ቅይጥ (ሃይብሪድ) ዘር፤ ጥሩ መገናኛ፤ መሰረተ ልማት፤ ትምህርት፤ የጤና አገልግሎት፤ እህል ለክፉ ቀን የሚቀመጥበት ጎተራ፤ በዝቅተኛ ወለድ የሚሰጥ ብድር፤ እውቀት፤ ምርምር፤ ገበያ፤ ወሳኝ ናቸው።

ለምሳሌ፤ ማሊ የተሻሻለ የሶርገም (ዘንጋዳ) ዘር ተጠቅማ **ምርቷን 40 በመቶ** አሳድጋለች። ሩዋንዳ One Acre Fund የተባለ የብድር ተቋም **ተጠቅማ ከ305,000** በላይ ለሚገመቱ፤ በአንድ ኤከረ፤ ሄክታር አይደለም፤ ለሚመኩ ዝቅተኛ አምራቾች “የማዳበሪያ፤ የምርጥ ዘር፤ የቴክኖሎጅ፤ የዜናና የእውቀት፤ የመገናኛና የብድር አገልግሎት” እንዲሰጥ አድርጋለች። ለማይችሉት የመንግሥት ድጎማ ታደርጋለች። እነዚህን ግብዓቶች የሚያገኙ ታናናሽ አምራቾች የገጠሩን ኢኮኖሚ ዘመናዊ እያደረጉት ነው። በምስራቅ ኤዢያ የሆነው “የገጠር አረንጓዴ አብዮት” በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች እየተሳካ ነው። አንድ የሩዋንዳ ገበሬ የቤተሰቡ ኑሮ ስለተሻሻለ እንዲህ ብሏል። “እኔ ህይወቴ ስለተሻሻለና የኃብቴ ባለቤት ስለሆንኩ ከገጠር ወጥቸ ወደ ከተማ ኑሮ አልሸጋገርም” ሲል የኢኮኖሚው መርህ አግባብ ያለው መሆኑን ያስመርበታል። እርግጥ ሩዋንዳ ዲሞክራስዊ አገር ናት ለማለት አይቻልም። የምታሳየው ማህበረሰባዊ ደህንነት ከኢትዮጵያ ይለያል። ሰብአዊ መብቶች ቢታፈኑም የዜጎች ህይወት እየተሻሻለ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት የለውም፤ ሰብአዊ መብቱ ተገፏል፤ በጠባብ ዘረኞች ይዋረዳል፤ በድህነት ይሰቃያል። አንዳንድ ሊቃውንት “ጥሩም አምባገነኖች” አሉ የሚሉት ለዚህ ነው።

ዘ ኢኮኖሚስት የኢትዮጵያን የመሬት ይዞታና አጠቃቀም ችግር እንዲህ ሲል ተችቶታል። “ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ የገጠርና ሌላ ኢኮኖሚ የሚተዳደረው ከላይ **ወደታች በሆነ የእዝና የቁጥጥር መርህ ነው።”** ማዳበሪይ፤ ብድርና ሌላ ግብአት የሚሰጠው በፖለቲካና በጎሳ ታማኝነት ነው። የዚህ ውጤት ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ሊገኝ የሚችለው የእርሻና ሌላ የምርት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑ ነው። ሩዋንዳ ምርቷን እያሳደገች ከውጭ እርዳታ ጥገኝነት ነጻ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች። ኢትዮጵያ ወደባሰ ጥገኝነት አምርታለች። ሩዋንዳ ለብዙ ወጣቶች ስራ ፈጥራለች። የእርሻዋ ክፍል የሚካሄደው እንደማንኛውም የቴሌቪዥን፤ የመኪና፤ የብረታ ብረት፤ የስሚንቶ ወዘተ ፋብሪካና ሌላ ዘመናዊ የምርት እንቅስቃሴ ወይንም ቢዝነስ ነው። የፖለቲካውና የኢኮኖሚው አመራር ጎጠኛና ብሄርተኛ ቢሆን ኖሮ ሁለገብና አገር አቀፍ፤ በተለይ አገር ተከል የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማካሄድ አይቻልም ነበር። በኢትዮጵያ የገጠር ኢኮኖሚው በፖለቲካ ቁጥጥር ስለተያዘና ሕዝቡ የመናገር ነጻነት ስለሌለው የፈጠራ መረጃ ይመረታል፤ የሌለውና ያልሆነው ምርትና የስራስ እድል ሆኗል ተብሎ ይሰበካል። የኢትዮጵያን የፈጠራ እርሻ ውጤት አከራካሪነት ወደጎን ትተን የስራ እድል ሁኔታን እንይ።

ህወሓቶች የስራ እድል በሽ በሽ ነው ይላሉ። ልክ ምርትም አድጓል፤ የሕዝብ ኑሮም ተሻሽሏል እንደሚሉት። በስራ እድል ራሳቸውን ከአሜሪካ፤ ከሳውዲ፤ ከኬንያ ወዘተ ጋር ያነጻጽራሉ፤ መረጃዎችን አያቀርቡም። የአሜሪካኖች ስራ አጥ መጠን 5 በመቶ ነው ሲባል የኢትዮጵያ ተመሳሳይ ወይንም ከዚህ በታች ነው ብለው ይከራከራሉ። የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ወደ አሜሪካ እንደሚጎርፍ ይክዳሉ። ይኼን ሚዛናዊ በሆነ ደረጃ የመረመረው የ**Mundi Index 2014** ዘገባ የኢትዮጵያ ስራ አጥነት መጠን **18 በመቶ** መሆኑን አስታውቋል። በዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከ101 ሚሊየን በላይ ነው።

**በ2014 መጨረሻ የተካሄደ የተባበሩት መንግሥታት ጥናት እድሜው ከ0-14** የሚገመተው ህዝብ መጠን **42** በመቶ፤ ከ15-64 የእድሜ ክልል የሚገኘው **55** በመቶ፤ ከዚህ እድሜ ክልል በላይ የሚገመተው ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። ሙንዲ ያቀረበው መረጃ አስራ ስምንት በመቶ የሚሆነው ስራ የሚፈልገው ህዝብ ስራ የለውም የሚል ነው። የዚህ ስራ ፈላጊ ህዝብ **መጠን 10 ሚሊየን** መሆኑ ነው። ስለዚህ፤

ህወሓቶች የስራ ፈላጊው መጠን ከሳውዲዎች፤ ከኬንያ ከሱዳኖችና ከአሜሪካኖች ዝቅ ይላል ሲሉ አስር ሚሊየን ህዝብ እንዴት ይኖራል ማለታቸው እንደሆነ ለህዝብ ቢገልጹ መልካም ነው። ሳውዲዎች የሕዝብ ዓመጽ ስለሚፈሩ ለእያንዳንዱ ዜጋ ድጎማ ያደርጋሉ፤ አሜሪካም እንደዚሁ ነው። አንባቢ በረሃብ የሚሰቃየውንና ስራ የሌለውን ሕዝብ ደምሮ የራሱን ግንዛቤ እንደሚያደርግ አምናለሁ።

ከአገር እንደ ጎርፍ የሚሰደደው ወጣት ትውልድ በህወሓቶች ስሌት ውስጥ እንደሌለ ግልጽ ነው። የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ድርጅት **<u>ቢያንስ 46 በመቶ</u>** የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ "ጦም አዳሪ (malnourished)" ነው ይላል። ይኼ ከሆነ ስራ የሌለው ህዝብ በልቶ አያድርም ማለት ጭምር ነው። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ስራ የሌለው ዜጋ ካለ ይህ ግለሰብ ራሱንና ቤተሰቡን ለመመገብ አማራጭ መፈለግ ግድ ይሆንበታል። አንድ ሰው በራሱ ህይወት ላፍ ፈርዶ ወደ አረብ አገሮች ወይንም ሌላ አይሰደድም። እንዲሰደድ ያስገደደው ቢያንስ ሁለት ሁኔታዎች እንደሚሆኑ እገምታለሁ፤

አንድ የስራ እድል አለመኖር፤

ሁለት የመብት መገፈፍ።

በአጭሩ፤ የፈለገውን ያህል የፈጠራ መረጃ ቢቀርብ የስራ እድል ያለመኖርና በልቶ ለማደር ያለመቻል ሃቅ በይፋ የሚታይ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ገጽታ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱና ሰብእነቱ ተከብሮ የስራ እድል ቢኖረውና በአገሩ በልቶ ቢያድር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይኮራል እንጅ ወደ ትችት አይገባም። ፍትህ ያለበትን አገዛዝ የሚተች ካለ ህሊናውን ይውቀሰው።

ለማጠቃለል፤ አስደናቂ የእድገት ውጤትና የውጤቱ ስርጭት አለ የሚለው የህወሓቶች ብሂል በማስረጃ ሊደገፍ አይችልም። ይህን የፖለቲካ መቆያ ጽንሰ ሃሳብ የሚያሽከረክሩ ባለሥልጣናትና ደጋፊዎች ተቃዋሚውን ከማውገዝ ይልቅ ሁለት ሁኔታዎችን መመለስ አለባቸው።

አንድ፤ በያመቱ ተገኘ የተባለው የእድገት ውጤት የፈጠራ ወሬ አለመሆኑን ከረሃብ፤ ከኑሮ ውድነት፤ ከስራ እድል እጥረት፤ ከስደተኛነትና ከጥገኝነት መቀነስ ጋር አያይዘው ለሕዝቡ መረጃ ማቅረብ፤

ሁለት፤ የእድገቱ መጠን እውነት ከሆነ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ያህል የእድገቱ ውጤት ተካፋይ ሊሆን እንደቻለና ጠባብ ብሄርተኞችና ጎሰኞች የእድገቱን ውጤት ለራሳቸው ጥቅም እንዳልማረኩት፤ ከሕዝብ ህይወት ሁኔታ በሚመጣ መረጃ ተደግፎ መልሶ ለሕዝቡ ማቅረብና ሕዝቡን ማሳመን ብሄራዊ ግዴታ መሆኑን መቀበልና ሃላፊነትን መወጣት።

ኢትዮጵያ በተከታታይ ለማኝና የምግብ ጥገኛ ለምን ትሆናለች? የሚለውን ጥያቄ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ማጤንና ማንሰላሰል ይኖርበታል። ስርዓቱ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አምባገነንም ሆኖ የኢትዮጵያዊያንን መሰረታዊ የኑሮ፤ የምግብ፤ የስራና ሌሎች ፍላጎቶች ለማሟላት ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለውም አነጋጋሪ ሆኗል። እነዚህ ጥያቄዎች በመንግሥት አፋኝነት፤ በክህደት፤ በበትር፤ በጥይት፤ በእስራትና በማሳደድ ሊመለሱ አይችሉም። ሊመልሳቸው የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። ለዚህም የስልጣን መጋራት አስፈላጊ ነው እላለሁ።